# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 110 ሰኔ 17 ቀን 2002 ገጽ 1


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የወቅቱ የግንቦት 7 የትግል ጥሪ

**“የጋራ ውርደት እንዲያከትም እብሪተኞችን በጋራ እምቢ እንበል፤ ዘረኛውና አዋራጁን የወያኔ ስርዓት ለማስወገድ በጋራ እንነሳ!!!:”**

**ጥርሱን አግጦ ለወጣ የአምባገነኖች የምርጫ ለበጣ ምላሹ “እምቢ ለመብቴ!!!” ብቻ ነው**

## የወያኔ አገዛዝ በቻይና መንግስት እርዳታ ኢሳት ቴሌቪዥንን እያፈነ መሆኑ ተዘገበ

ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ በቅርቡ የተቋቋመውን የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ወይም ኢሳት ስርጭት ማፈን የቻለው በቻይና መንግስት እርዳታ መሆኑ ተዘገበ።

አዲስ ነገር አንላይን የተባለው የዜና ድረ-ገጽ ማክሰኞ እለት ባወጣው ዘገባ፣ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ የተባለውና በወያኔ ሙሉ ቁጥጥር ስር የሚገኘው የመንግስት ቢሮ ኢሳትን የማፈኑን ተግባር እንደሚያካሄድ ገልጿል። መስሪያ ቤቱ ኢሳትን ለማፈን ዝግጅት ማድረግ የጀመረውም የቴሌቪዥን ጣቢያው መቋቋሙን ባሳወቀ በሁለተኛ ቀኑ ከመለስ ዜናዊ በደብዳቤ የመጣን ትእዛዝ ተከትሎ መሆኑም ታውቋል።

ዘረኛው አምባገነን መለስ ዜናዊ አዲሱ የቴሌቪዥን ድርጅት የግንቦት 7 ሊቀመንበር ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ንብረት ነው ብሎ ያምን ኖሯል። በደብዳቤውም፥ መስሪያ ቤቱ በተቻለው መንገድ ሁሉ የቴሌቪዥን ስርጭቱን እንዲያስቆም ወይም እንዲገድብ ያዘዘ ሲሆን፤ በዚህም መሰረት አገዛዙ ከቻይና መንግስት እርዳታ ጠይቋል። የቻይና መንግስትም በረዥም ጊዜ ብድር የሳተላይት ስርጭት ማፈኛ መሳሪያ እንደላከ እና መሳሪያውም ወዲያው ስራ ላይ እንደዋለ አዲስ ነገር ዘግቧል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## በዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ስር የምትገኘው ኢትዮጵያ ከወደቁ አገራት ተርታ ለመሰለፍ ጥቂት ከቀራቸው አገሮች አንዷ ነች ተባለ

“ፎሬን ፖሊሲ” በመባል የሚታወቀው ድርጅት ሰሞኑን ባወጣው አመታዊ “የወደቁ አገራት” መመዘኛ ሪፖርት፣ መንግስት የሌላትን ሶማሊያን አንደኛ ደረጃ ላይ ሲያኖር፣ ኢትዮጵያን አስራ ሰባተኛ ላይ አስቀምጧል። አጠቃላይ ውጤቷም ከአለፈው አመት መክፋቱን ገልጿል።

በዚህ ሪፖርት፥ አገራት ባላቸው መረጋጋት፤ የሰብአዊ መብት ሁኔታ፤ የዜጎች ለስደት መዳረግ፤ የኢኮኖሚ እድገት ማሽቆልቆል፤ የመንግስት ተቀባይነት ማጣት፤ እና በመሳሰሉት መስፈርቶች ይለካሉ። በዚህ መሰረት አንደኛዋ ሶማሊያ 114.3 አሉታዊ ውጤት ሲሰጣት፤ 17ኛዋ ኢትዮጵያ 98.8 አግኝታለች። ከዚህም የተነሳ “አደገኛ ሁኔታ” ላይ ካሉ እና የወደቁ ለመባል አንድ ደረጃ ከሚቀራቸው አገሮች ተርታ ተመድባለች።

በተያያዘ ዜና፥ በዚሁ ተቋም ድረ-ገጽ ላይ “የከፉዎች ከፉ” በሚል ርእስ የአለማችንን ሃያ ሶስት አምባገነኖች የሚዘረዝር ጽሁፍ ያወጡት ጋናዊ ምሁር ፕሮፌሰር ጆርጅ አይተይ፤ መለስ ዜናዊ ከስልጣን ካስወገደው ከመንግስቱ ሃይለማርያም የባሰ ነው ሲሉ ፈርጀውታል።

## በአዲስ አበባ የወያኔ አገዛዝ የጸጥታ ሃይሎች በርካታ ወጣቶችን እያሰሩ መሆኑ ታወቀ

ከግንቦት 15ቱ የምርጫ ተውኔት በኋላ በርካታ ወጣቶች በዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ የጸጥታ ሃይሎች እየታሰሩ መሆናቸውን የግንቦት 7 ድምጽ ሪፖርተር ከአዲስ አበባ ዘግቧል።

ዘጋቢያችን አጠናቅሮ እንደላከው መረጃ፥ አንዳንድ ያናገራቸው ቤተሰቦች ወጣቶች ልጆቻቸው በደህንነት ሰራተኞች ከተወሰዱ በኋላ የት እንደደረሱ አያውቁም።

ፍጹም አምባገነናዊነቱ እርቃኑን ሲወጣበት ለየት ወዳለ የስጋት ደረጃ የደረሰ የሚመስለው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ፤ የስልላ እንቅስቃሴውን የበለጠ ማጠናከሩ ታውቋል። አንዳንድ ወጣቶች በገላጣ ቦታዎች ሆነው ስለ ምርጫው ሲያወሩ በመገኘታቸው ብቻ መታሰራቸውን ዘጋቢያችን ለዝግጅት ክፍላችን ባደረሰው መረጃ አስረድቷል።

ግዜ ግንቦት 7 ዜና

## የመኢዴአፓ ሊቀመንበር ለነጻነት የሚደረገውን ትግል እንደሚቀላቀሉ ገለጹ

በምህጻረ ቃሉ መኢዴአፓ እየተባለ የሚጠራው የመላው ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ፓርቲ ሊቀመንበር አቶ ዘለሌ ጸጋስላሴ ለነጻነት የሚደረገውን ትግል ለመቀላቀል ውሳኔ ላይ መድረሳቸውን ገለጹ። መኢዴአፓ በኢትዮጵያ ውስጥ በተካሄደው የምርጫ ድራማ ቀደም ብሎ ለመሳተፍ ሲንቀሳቀስ የቆየ ነገር ግን የገዢው ፓርቲ ከእለት እለት ያደርግ የነበረው አፈናና ጫና አሳሳቢ ደረጃ ላይ ሲደርስ በምርጫው ላለመሳተፍ ውሳኔ ላይ ከደረሱት ፓርቲዎች አንደኛው ሲሆን በጥቂቱም ቢሆን በተካሄዱት የምርጫ ተብየው የምረጡኝ ፉክክሮች የገዢውን ፓርቲ ችግሮች በማጋለጥ ሂደቱ ከታወቁት ተቃዋሚ ፓርቲዎች ውስጥ አንደኛው በመሆኑ በገዢው ፓርቲ ጥርስ ውስጥ ገብቶ እንደነበረ አይዘነጋም።

አቶ ዘለሌ ጸጋ ስላሴ ከግንቦት ሰባት ራዲዮ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ፓርቲያቸው በሃገር ውስጥ ምናልባት ይቻል እንደሆን በሚል ተስፋ በሰላማዊ ትግል የገዢውን ፓርቲ ለመጣል ሲንቀሳቀስ እንደነበር ገልጸው ይሁን እንጂ በ2002ቱ የኢትዮጵያ ምርጫ ተብየ ሂደት በተግባር የታዩት ኩነቶች በሙሉ የወያኔን አገዛዝ በሰላማዊ ትግል በተለይም በምርጫ ለመጣል የሚደረገው ትግል ያለቀለት ጉዳይ መሆኑንና በኢትዮጵያ ላለውም አሳሳቢ ሁኔታና ችግር መፍትሄ ማግኘት የሚቻለው በቅድሚያ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ነጻነቱን ማረጋገጥ ሲችልና ለዚህም ነጻነት ሁሉን አቀፍ በሆነ ትግል ውስጥ ሲሳተፍ ብቻ እንደሆነ ገልጸዋል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ባለፉት አስር አመታት ለስደት የዳረጋቸው ጋዜጠኞች ቁጥር ከአለም አንደኛው ነው ተባለ

ሲ.ፒ.ጄ. የተባለው የጋዜጠኞች መብት ተሟጋች ድርጅት ባለፈው ሐሙስ በለቀቀው ሪፖርት በአለፉት አስር አመታት ለስደት የሚዳረጉ ኢትዮጵያውያን ጋዜጠኞች ቁጥር ከአለም አንደኛ ነው ብሏል።

በነዚህ አስር አመታት ስልሳ ሁለት ኢትዮጵያውያን ጋዜጠኞች አገራቸውን ጥለው የተሰደዱ ሲሆን፤ ይህም እስርን፣ ጥቃትን እና ማስፈራራትን ሽሽት እንደሆነ ታውቋል። ባለፈው አመት ብቻ አስራ አምስት ጋዜጠኞች ከኢትዮጵያ እንደሸሹ እና ይህም ነፃው ፕሬስ ያለበት ሁኔታ እየከፋ ስለመሄዱ ማስረጃ ነው ሲል ሪፖርቱ ገልጿል።

የወያኔ አገዛዝ የግል መገናኛ ብዙሃንን ነፃነት የሚገድብ ህግ ከማውጣት አንስቶ ጋዜጠኞችን እንዳሻው በማሰር፤ በመክሰስ እና በማስፈራራት ከሞላ ጎደል ነፃውን ፕሬስ መዝጋቱ ይታወቃል። ከኢትዮጵያ ውጭ የሚገኙ ገለልተኛ እና ተቃዋሚ መገናኛ ብዙሃንም ለኢትዮጵያውያን እንዳይተላለፉ ከፍተኛ የአፈና ዘመቻ ያካሂዳል።

በተያያዘ ዜና አገዛዙ ሄዘር መርዶክ የተባለችን የአሜሪካ ድምጽ ዘጋቢ ከአገር ማስወጣቱ ታውቋል። የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባር ወይም ኦብነግ የወያኔ ጦር በኦጋዴን 71 ንጹሃን ዜጎችን ገድሏል በሚል በመግለጫው ያወጣውን ክስ ለመመርመር ምስራቅ ኢትዮጵያ የተጓዘችው ሄዘር መርዶክ ባቢሌ ከተማ አካባቢ ለሁለት ቀናት መታሰሯን ብሉምበርግ የዜና አውታር ዘግቧል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብት ከፍተኛ ኮሚሽነር በኦጋዴን የተፈጸመን የጦር ወንጀል እንዲመረምሩ ጥሪ ቀረበላቸው

“ሶሳይቲ ፎር ትሬትንድ ፒፕል” ወይም በምህፃረ ቃል ኤስ.ቲ.ፒ. የተባለ የሰብአዊ መብት ተከራካሪ ድርጅት በኦጋዴን የዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ጦር ገድሏቸዋል ስለተባለው 71 ንጹሃን ዜጎች ገለልተኛ ምርመራ እንዲያደርጉ ለተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብት ከፍተኛ ኮሚሽነር ናቫነተም ፒሌይ ጥሪ አቀረበ።

ድርጅቱ ተገደሉ ከተባሉት ሰዎች ውስጥ የሰላሳ አራቱ ስም ዝርዝር እንደደረሰው እና ያንንም ለተባበሩት መንግስታት ማስተላለፉን ገልጿል። ኤስ.ቲ.ፒ. ጉዳዩ መለስ ዜናዊ የጂ20ን ስብሰባ ለመካፈል ወደ ካናዳ ከመሄዱ በፊት እንዲጣራ ጠይቋል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የወያኔን የመረጃ አፈና ለመበጣጠስ አዕምሮዓችንን እናሰራ፣ ኪሳችንን እንፈትሽ፣ ቆርጠንም እንነሳ!!!

መረጃ ኃይል ነው። መረጃ እውቀትና ሃብትም ጭምር ነው። በሃያ አንደኛው ክፍለ-ዘመን ለልማት ከሚያስፈልጉ ግብዓቶች መረጃ ቀዳሚው ሥፍራ ይዟል። መረጃን አፍኖ ትምህርትን፣ የጤና አገልግሎትን፣ ንግድን እና ሌሎችን የልማት ሥራዎችን በጥራት ማሳደግ አይቻልም። መረጃን አፍኖ መልካም አስተዳደርና ፍትህን ማስፍን የዜጎችን ዲሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶችን ማስከበር የማይታሰብ ነው። ከሁሉም በላይ ደግም መረጃ ማግኘት የዜጎች መብት ነው። መረጃ የማግኘት መብቱ የተገፈፈ ዜጋ መሰረታዊ የሆነ የዜግነት መብቱ ተገፏል፤ ከዚህም ጋር ስለ እራሱ የማወቅንምን ሆነ ራሱን የማሳደግ መብቱ ተነፍጓል።

መረጃን ጠቅልሎ ይዞ ለእኩይ ተግባራት ማዋል የአምባገነን ገዢዎች ሁሉ የጋራ ባህርይ ነው። መለስ ዜናዊም የአልባንያውን ኢንቨር ሆዣ ከመሳሰሉ የእውቀት ጌቶቹ በተማረው መሠረት የኢትዮጵያን ሬድዮና ቴሌቪዥን ተቆጣጥሮ ተቋማቱን ወደ ውሸት ማምረቻና ማሰራጫነት ቀይሯቸዋል።

በወያኔ ሙሉ ቁጥጥር ሥር የሚገኘው የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የሚያመርታቸውና የሚያሰራጫቸው ውሸቶች ብዛትና ዓይነት ተነግሮ አያልቅም። ቴሌቪዥኑንና ራዲዮው ዴሞክራሲና ብልጽግና በሃገሪቱ በሽብሽ እንደሆኑ ይናገራሉ። ከቴሌዥኑና ከሬድዮው ጣቢያዎቹ ደጃፍ ግን ዜጎች ግንባራቸው በአጋዚ ጥይት እየፈረሰ ይደፋሉ። የሚላስ የሚቀምስ ያጡ፤ ቀኑ የጨለመባቸው ወጣቶች የመከራ የጎዳና ሕይወት እዛው እደጃፍ ላይ ይገፋሉ። በቴሌቪዝኑ መስኮት ገበሬዎች ሚሊዮነሮች ሆነው ሜዳልያ ይሸለማሉ። በየገጠሩ የምግብ እርዳታ ካላገኘ ለጥቂት ቀናት ስጋውን ከነፍሱ አጣብቆ ማደር የማይችለው ዜጋ ቁጥር ወደ 15ሚሊዮን አሻቅቧል። ገዳዮች ከሳሾች ሆነው ሟቾች ወንጀለኞች ተደርገው ይቀርባሉ። ሃገረ ከሃዲዎች ሀገር ወዳዶችን በሃገር ክህደት ከሰው ወህኒ አጉረው ይታያሉ። በወያኔ እጅ የሚገኙ የመገናኛ አውታሮች የተጠደመዱት ድንጋይን ዳቦ አድርጎ በማቅረብ፣ በወንፊት ውሃ ቀዳን፣ ግመልን በመርፌ ቀዳዳ አሾለክን፣ ነጭ ኑግ ጥቁር ወተተና የዶሮ ጥርስ በመለስ ዜናዊ ቆራጥ አመራረና በወያኔ ልማታዊ መንግስት ጥረት ተመረቱ የሚል ሃፍረተቢስ ቅጥፈት በማሰራጨት ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ አማራጭ መረጃዎችን ከኢንተርኔት ድረገፆች እንዳያገኝ ወያኔ ከፍተኛ ገንዘብ እያፈሰሰ ዋና ዋናዎቹን ድረገፆች ዘግቷል። በኅትመት ሚዲያና በጋዜጠኖችም ላይ የሚደረገው አፈና ተፋፍሞ ቀጥሏል። ሰሞኑን ከተደመጡ የወያኔ ፀረ-መረጃ ሥራዎች በአሜሪካ ድምፅ ጋዜጠኛ ሄትኸር መርደክ ላይ የደረሰው ነው። ይህች ጋዜጠኛ የቱሪዝብ መስህብ ስለሆኑት ለማዳ ጅቦች ለመዘገብ ወደ ሃረር በመጓዟ እግረ መንገዷን እዚያ ያለውን ጉዳችንን ታወጣብን ይሆናል በሚል ስጋት ከአገር እንድትባበር ተደርጓል።

ይህ ሁሉ ያው የምናውቀው የአፈናና የውሸት ፍብረካ ታሪክ ነው። ወያኔ እስካለ ድረስ እየባሰ እንጂ እየቀነሰ አይሄድም። መሠረታዊው ጥያቄ "ምን ይደረግ?" የሚለው ነው።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ለዚህ ጥያቄ ያለውን ምላሽ በተደጋጋሚ ገልጿል። እንደ ግንቦት 7 እምነት በኢትዮጵያ ውስጥ ፈጣንና አዎንታዊ ለውጥ ለማምጣት የነፃ ሚዲያ መኖር ወሳኝ ነው። የወያኔን የመረጃ አፈናን መበጣጠስ ያለብን እኛው ነን። ይህን ማድረግ ደግሞ ይቻላል!!! በቅርቡ ስራውን የጀመረው የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዝን (ኢሳቴ) ይህን በተግባር አረጋግጦልናል። ኢሳቴ ሁለት ታላላቅ ጉዳዮችን አሳይቶናል -

1. የወያኔ የመረጃ አፈና ሊሰበር እንደሚቻል በተግባር አሳይቶናል። ወያኔ በኢቲቪ ላይ ከሚያፈሰው አንድ ሺህኛ እንኳን በማይሆን ወጪ ከኢቲቪ እጅግ የተሻሉ ማራኪና አስተማሪ ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት የሚቻል መሆኑን አስመስክሯል።
2. ለሃቅ፣ ለፍትህ፣ ለነፃነት፣ ለሰብዓዊ መብቶች መከበር መቆም የቱን ያህል በሕዝብ እንደሚያስወድድ አሳይቶናል። ኢሳቴ ገና ከመነሻው የሕዝብ ቴሌቪዥን ሆኗል።

የኢሳቴ መወለድ ወያኔን በእጅጉ አስደንግጧል።ውሸት ብቻ መናገር የለመደበት ተቋም እውነትን ብቻ ከሚናገር ተቋም ጋር መፎካከር እንደማይችል ግልጽ ነው። ስለሆነም ወያኔ የሕዝብን ሃብት በማፍሰስ የሳተላይት ስርጭቶችን የሚረብሹ ሞገዶችን በውድ ዋጋ እየተከራየ ኢሳቴን ማወክ ጀመረ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጎኑ ቆሟልና ኢሳቴ የደረሰበትን ጥቃት የመቋቋም አቅም ገንብቶ ይመለሳል ብለን ተስፋ እናደርጋለን። መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በዚህ ረገድ ለኢሳቴ ያለውን ድጋፍ እንዲቀጥል፤ በፋይናንስ፣ በሙያ፣ በተቻለን ነገር ሁሉ ኢሳቴን እንድንደግፍ ጥሪዓችንን እናቀርባለን።

ከዚህ በተጨማሪም የወያኔን ጩኸትና ሁከት የሚቋቋም በየእለቱ የሚተላለፍ ለእውነት፣ለፍትህ፣ ለነፃነትና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር የቆመ ሁነኛ የሕዝብ ሬድዮ ጣቢያ በአስቸኳይ መቋቋም ይኖርበታል። ለገጠሩ ሕዝባችን በአስተማማኝ ሁኔታ መድረስ ይኖርብናል። ግንቦት 7 ኢትዮጵያዊያን በዚህም ጉዳይ ላይ እንዲያስቡበት ያበረታታል።

በተመሳሳይ ሁኔታም በህትመትም ዘርፍ ወርሃዊ መጽሄትንና ሳምንታዊ ጋዜጣን ለኢትዮጵያዊያን ማድረስ የሚቻልበት ሁኔታ መፈለግ ይኖርበታል። የወያኔን የመረጃ አፍና ለመበጣጠስ የህንጻዎች ግድግዳዎችና ለመጻፊያነት የሚመቹ የሃገራችን ተራሮች፣ ኮረብታዎችና ገደሎች በቀለም መሸፈን ይኖርባቸዋል። የወያኔ ጉድ የሚያጋልጡ፣ በኅቡዕ የሚዘጋጁና የሚበተኑ በራሪ ወረቀቶች በየገበያው ቦታ፣ በየትምህርት ቤቱ እና በየቤተ አምለኮው መበተን ይኖርባቸዋል።

የወያኔን የመረጃ አፈናን መበጣጠስ እንደሚቻል ኢሳቴ ጥሩ ማስረጃ ነው። መረጃ የማግኘት መብታችንን ማንም አምባገነን ሊያፍነው እንደማይችል ለመለስ ዜናዊና ለተባባሪዎቹ በመተባበር እናሳያቸው። የነፃነት እሳት መንበልበል ይኖርበታል። ለዚህ ክቡር ዓላማ ሁላችንም አዕምሮዓችንን እናሰራ፣ ኪሳችንን እንፈትሽ፣ ቆርጠንም እንነሳ!!! !

### ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!

## የተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብት ከፍተኛ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባር ባለፈው ወር ሃረር አካባቢ በመልቃላ ከተማ በወያኔ ጦር ላይ ጥቃት ከፈጸመ በኋላ፤ የአገዛዙ ወታደሮች ፋፈን፣ ፋርሶ፣ ጎራይ፣ ባምባስ፣ እና ገላልሼ ወደተባሉ መንደሮች በመሄድ አዛውንቶችን እና ገበሬዎችን በቤተሰቦቻቸው ፊት በተኩስ መግደላቸውን የአይን ምስክሮች እንደተናገሩ ኤስ.ቲ.ፒ. ገልጿል። ጥቃቱን ተከትሎ በርካታ ኢትዮጵያውያን ከአካባቢው መፈናቀላቸውም ታውቋል።

የወያኔ አገዛዝ ለዜጎቿ በቂ የህግ ጥበቃ ስለማያደርግ፤ ኢትዮጵያ ለህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ዋና ምንጭ ከሆኑ ሃገራት አንዷ ነች ተባለ።

የአሜሪካ መንግስት የውጭ ጉዳይ ቢሮ በዚህ ሳምንት ባወጣው አመታዊ ሪፖርት፤ የኢትዮጵያው አገዛዝ የህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባዎችን ለመጠበቅ የተቀመጠውን ህግ አነስተኛ መስፈርት ባለማሟላቱ ኢትዮጵያ ይህ ግፍ በከፍተኛ ደረጃ ከሚካሄድባቸው አገሮች መካከል አንዷ ነች ብሏል።

ሪፖርቱ ኢትዮጵያ ለግዳጅ የጉልበት ስራና ለሴተኛ አዳሪነት ሊዳረጉ ከአገር አገር ለሚጓጓዙ ዜጎች ምንጭ ሃገር ነች ብሏል። ከተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የመጡ ኢትዮጵያውያን ሴት ልጆች በመካከለኛው ምስራቅ አገራት እና በሱዳን ለግዳጅ የጉልበት ስራ እንደሚውሉ የገለጸው ሪፖርት፤ በተለይ በመካከለኛው ምስራቅ አገራት የሚሰሩ ኢትዮጵያውያን መደብደብ፣ አስገድዶ መደፈር፣ ደሞዝ እና እንቅልፍ መከልከል፤ እቤት ውስጥ መታፈን፤ እስር እና ግድያ እንደሚደርስባቸው ዘርዝሯል።

አንዳንዶቹ ሴቶች በየደረሱባቸው አገራት በግዳጅ በሴተኛ አዳሪነት ስራ እንዲሰማሩ እንደሚደረጉም በሪፖርቱ ተገልጿል። ብዙዎቹ በተስፋ መቁረጥ ለአእምሮ በሽታ እንደሚዳረጉና፤ አንዳንዶቹም እራሳቸውን እንደሚገድሉ ታውቋል።

ከሴቶቹ በተጨማሪ የተወሰኑ ኢትዮጵያውያን ወንዶችም በየአመቱ ወደ መካከለኛው ምስራቅ እና አንዳንድ አፍሪካ አገራት በመሰደድ ለግዳጅ የጉልበት ስራ ይሰማራሉ።

ሪፖርቱ የኢትዮጵያ መንግስት ሁኔታውን ለማሻሻል እየጣረ ነው ቢልም፤ በበርካታ አገራት የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች

በያገራቱ ያሉ የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች ለአቤቱታዎቻቸው ጆሮ እንደማይሰጡ በተለያዩ ጊዜያት ተናግረዋል። አንዳንድ የገዢው ፓርቲ ሰዎችም ወደ መካከለኛ ምስራቅ አገራት ሴት ሰራተኞችን በመላክ ስራ ትርፍ እንደሚያገኙ ይነገራል።

ኢትዮጵያውያን በአለም ላይ በከፍተኛ ቁጥር ከሚሰደዱት ህዝቦች ተርታ ሲሆኑ፤ ሂውማን ራይትስ ዋች የተባለው የሰብአዊ መብት ተከራካሪ ቡድን ከወራት በፊት ባወጣው ሪፖርት፤ በሁለት አመት ውስጥ መቶ ሺህ የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን እና ሶማሊዎች ወደ የመን ብቻ መሰደዳቸውን ገልጿል። ኢትዮጵያውያን በታላቅ ቁጥር አገራቸውን ጥለው እንዲሰደዱ የሚያደርጋቸው ዋና ምክንያት በአገሪቱ ውስጥ ያለው ድህነት እና የፖለቲካ እንግልት እንደሆነ ይታወቃል።



የፖስታሳጥን ቁጥር ፦ POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

# ምርጫ 2002 በተመለከተ የግንቦት 7 አቋም ማብራሪያ

**(ይህ መግለጫ ባለፈው ዓመት በ2001 ዓ.ም በነሐሴ ወር የወጣ ሲሆን ከምርጫ ጋር በተያያዘ ያለፍንበትንን፣ የአሁኑን የወደፊቱንም በጥልቀት የዳሰሰ በመሆኑ በድጋሚ እንዲነበብ እንጋብዛለን) (ክፍል 2)**

## 2.2 ለመሆኑ ዓለም የሚያውቃቸው የእውነተኛ ውድድር ምርጫ መለያዎች ምንድር ናቸው?

ዲሞክራሲያዊ የምርጫ ሥርዓት የግድ ነፃ (free) ፍትሃዊና (fair) ተአማኒነት ያለው (credible) የፖለቲካ ሜዳ ተፈጥሮ፣ የፖለቲካ ቡድኖች የሚወዳደሩበት መድረክ ነው። ለዚህም:-

- አስመራጩ (የምርጫ አስፈፃሚው) አካል ከአንድ ፓርቲ ቁጥጥርና ተጽእኖ ነጻ ሆኖ የተደራጀ፣ በነፃ አሠራርና በገለልተኛነት ሥነ ምግባር የዳበረ ቡድን መሆን አለበት፡፡
- የመንግሥት ሥልጣን በግልጽ በተደነገጉ በሥልጣን መባለግ እንዳይኖር በሚያደርጉ ሕጎች የተከፋፈለና ተጠያቂነት ያለበት፤ ይህም በተግባር የተመሠከረለት መሆን አለበት፡፡
- የአገሪቱ የፍትህ ሥርዓት በቅልጥፍና፤ በእኩልነትና ከሕግ አስፈጻሚው ነፃ በሆነ መልኩ ሲሠራ የታዬ መሆን አለበት፡፡
- የመንግሥት ወታደር፤ ፖሊስ፤ የፀጥታና እንዲሁም ሲቪል አስተዳደሩ ከፖለቲካ ፓርቲዎች ቁጥጥር ውጭ መሆን አለበት፡፡
- የመንግሥት ሀብት ተቀናቃኝ ፓርቲዎችን ማዳከሚያ፣ በምርጫ አሸናፊ ሆኖ ለመውጣት መጠቀሚያ፣ ዜጎች የገዥው ፓርቲ አባላት እንዲሆኑ የመግዣና የማስገደጃ መሣሪያ መሆን የለበትም፡፡
- የመንግሥት ሚዲያም ለሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶችና ለሁሉም ዜጎች መገልገያ በሚሆንበት መልኩ ከፖለቲካ ፓርቲዎች ነጻና ገለልተኛ በሆነ መንገድ መደራጀት ይኖርበታል፡፡

እነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች ባልተሟሉበት አገር እንኳን እንደ ወያኔ ባለ ለአስራ ስምንት ዓመታት በማጭበርበር የታወቀ ገዥ ቡድን ቀርቶ በሌሎችም ለዘብተኛ አገዛዞች በሚገኙባቸው አገሮች እንኳን ሃቀኛ ውድድር ያለበት ምርጫ ማድርግ እንደማይቻል ተደጋግሞ ታይቷል። ከእዚህ ተነስተን እስኪ ወያኔ በምርጫ ግጠሙኝ እያለ በተቃዋሚዎች ላይ የሚፏልልበት የአገራችንን ወቅታዊ የምርጫ ሁኔታ ምን እንደሚመስል እንመልከት፤

- አገራችን በመለስ ፈቃድ ብቻ የሚንቀሳቀስ የምርጫ ቦርድና መለስ እንዳሻው የሚሾማቸውና የሚሽራቸው የምርጫ ቦርድ አባላት አሏት፡፡ ከእነዚህም መሃል አብዛኛዎቹ የወያኔ ካድሬዎች ናቸው፡፡
- አገራችን በወያኔ በጎ ፈቃድ ብቻ የሚዘወር የወያኔ የፕሮፓጋንዳ መሣሪያ የሆነ የፌደራልና የክልል መንግስታት መገናኛ ብዙሃን ያለባት አገር ናት፡፡ የግል የተባሉ ጥቂት ራድዮ ጣቢያዎች በሙሉ በወያኔ ካድሬዎችና በወያኔ ካፒታልና ፈቃድ የተቋቋሙ ናቸው፡፡ የግል ጋዜጦችም በወያኔ አፋኝ የፕሬስ ህግና የአፈና ተቋማት በነጻነት እንዳይዘግቡ የቀፈደዱ ናቸው፡፡
- አገራችን መለስ ዜናዊ በአንድ ቀን ውስጥ የፈለገውን (የገዛ ህገ-መንግሥቱን ጭምር የሚጥስ) ህግ ለማውጣት የሚያስችለው በመለስ የሚታዘዝ ፓርላማ ያለባት አገር ናት፡፡ መለስ ዜናዊ ለዳኞች ስልክ ደውሎ፣ የብይን ውሳኔያቸው ምን መሆን እንደሚገባው ትእዛዝ የሚሰጥባት ሃገር ናት፡፡ ዳኞች፣ አቃቤ ህጎችና መረጃ አቅራቢ ፖሊሶች በሙሉ የወያኔ ካድሬዎች ናቸው፡፡
- አገራችን፣ መለስ የምርጫ ውጤት ካልተስማማው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የሚያውጅባት፣ በመለስ ትእዛዝ ሰላማዊ ስልፈኞችን እያነጣጠረ ግንባርና ልብ ላይ የሚተኩስ ነብሰ ገዳይ፣ ልዩ ጦር መኖሩ በግልጽ የታየባት አገር ናት፡፡
- <u>**ከሁሉም በላይ**</u> ሃገራችን በግምት ሳይሆን በተግባር በምርጫ 97 እንደታየው፤ ነፃ ምርጫ ከተደረገ የወያኔ መንግሥት ከስልጣን ሊወገድ የሚችልባት አገር ናት።

ከላይ የጠቀስናቸው ነጥቦች በአገራችን ነጻና ገለልተኛ የምርጫ ቦርድ፣ ፕሬስ፣ የፍትህ ሥርዓት፣ የፖሊስ፣ የደህንነትና የመከላከያ ኃይል አለመኖራቸውን የሚረጋግጥ ነው፡፡ እነዚህ ተቋማት የሉም ማለት ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ ሊኖር አይችልም ማለት ነው፡፡ ይህ ድምዳሜ በሂሳብ 1 ሲደምር 1 ሁለት ይሆናል ከሚለው ሎጂክ ምንም ልዩነት የሌለው ነው፡፡ በምንም ምክንያት የሚለወጥና የሚቀየር አይደለም፡፡ የመጨረሻው ነጥብ ደግሞ የሚያሳየን፤ እውነተኛ የሕዝብ ወገን የሆኑ ሁሉ በኢትዮጵያ ስለምርጫ ሲያስቡ የማሸነፍ እድላቸው በተግባር የታየና የሚቻል መሆኑን እራሳቸውም አምነው ለሕዝቡም ይህንን ሁኔታ በመግለጽ መሳተፍ የሚገባቸው መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡ የማሸነፍ እድላቸው ዛሬ ጠቦ የሚታየው ወያኔ ከግንቦቱ 1997 ምርጫ በኋላ የወሰዳቸው የእመቃ እርምጃዎች ውጤት እንጂ ድርጅቶቹ ከወያኔ በማነሳቸው ህዝቡም ወያኔ ላይ የነበረው ምሬት በድንገት ወደ ፍቅር በመቀየሩ እንዳልሆነ ማወቅ ይኖርባቸዋል፡፡ ከእዚህ ተነስተው ለማናሸንፍበት ምርጫ ለምን እንገባለን የሚል የተስፋ መቁረጥ አቋም ከመውሰዳቸው ወይም ለማናሸንፍበት ምርጫ ወያኔን የወሰነልን ወንበር ተቀብልን መሰንበት የሚል አደገኛ ውሳኔ ላይ ከመድረሳቸው በፊት በነጻና በፍትሃዊ ምርጫ ወያኔን ከሥልጣን ማባረር እንደሚችሉ በራሳቸው መተማመን ይኖርባቸዋል፡፡ ምርጫ 97 ያስተማረን ቁም ነገር ቢኖር በተቃዋሚዎች ላይ ትልቅ ንቀት የነበረው ወያኔ በራሱ ተማምኖ በከፈታት የዴሞክራሲ ቀዳዳ ተቃዋሚዎች ወያኔን በቀላሉ ከሥልጣን ሊያባርሩት እንደሚችሉ ነው፡፡ ችግሩ ያለው የዴሞክራሲ ምህዳሩ መጥበብ ላይ እንጂ ህዝብ በወያኔ ላይ መማረሩን ስላቆመ እንዳልሆነ መተማመን ያስፈልጋል፡፡ ሕዝብ የነጻ ምርጫ እድል ቢሰጠው አሁንም ከ1997ቱ በከፋ መልኩ ወያኔን የሚተፋወ መሆኑን መገንዝብ ተገቢ ነው፡፡ የዴሞክራሲ ምህዳሩ ቢሰፋ የነጻና የፍትሃዊ ምርጫ ሂደት ቢጀመር ተቃዋሚ ፓርቲዎች በአጭር ግዜ ውስጥ ተሰባስበው በጋራ ወያኔን ገጥመው ሊያሸንፉት የሚችሉበትን መርሃ ግብር መዘርጋት፣ የሕዝብንም ድጋፍ ማግኘት እንደሚችሉ በራሳቸው ላይ መተማመን ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ይህ በተግባር በ1997ቱ ምርጫ የታየ ሰለሆነ ተቃዋሚዎች ወያኔ የሚነዛውን የቅስም ሰበራ ፕሮፖጋንዳና ጭቆና ራሳቸውም ሆኑ ሕዝብ መቋቋም እንዲችል በጋራ መታገል ይኖርባቸዋል። በተጻራሪው መንግሥት አሁን ካለው የመጨቆን አቅም ተነስተው ግን ማሸነፍ እንደማይቻል ማሰብ ትልቅ ስህተት ነው። ከዚህ የተሸናፊነት መንፈስም በመነሳት የመለስ-በረከት ቡድን አስልቶ የፈቀደልንን ወንበር መያዝ መሻሻል ነው ብለው ካሰቡ ደግሞ የከፋ ስህተት ይፈጽማሉ፡፡ እንዲህ አይነቱ ውሳኔ የሀገሪቱን ሁኔታና የሕዝብን ፍላጎትና ችሎታ አለመረዳት ይሆናል። ሰሙ-ጥሩ የተቃዋሚ ሰዎች ወያኔን አጅበው ለወያኔ አሸናፊነት በተመቻቸ ምርጫ ከገቡ የዚህ ተግባር ዋና ውጤቱ በሀገራችን ውስጥ በዘር መድሎና በአምባገነንነት ላይ የተዘረጋውን ሥርዓት እድሜ ማራዘም ይሆናል።

## 3. ወያኔና የ2002 ምርጫ

የ2002ቱ ምርጫ ገና አንድ ድምፅ ከመሰጠቱ በፊት ወያኔ አሸናፊነቱን የተረጋገጠ ለማድረግ በሁለት ምዕራፎች የተከፋፈለ መርሃ ግብር ነድፎ መነቃነቅ ከጀመረ ሰንብቷል። የመጀመሪያው ምዕራፍ የተቃዋሚ ኃይሎችንና የሲቪል ማኅበራትን ማዳከም እና የሕዝብን ቅስም መስበር ሲሆን፤ ሁለተኛው ምዕራፍ ደግሞ እራሱ መጥኖ በሚከፍታት ጊዜና ሁኔታ የአስመሳይ ምርጫ "ውድድርን" ማኪያሄድ ነው።

ተቃዋሚዎችን በማዳከም ዙሪያ ወያኔ እስካሁን ያደረጋቸው ዋና ዋና እርምጃዎች የሚከተሉትን ይመስላሉ፤

- ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ደግፈዋል፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን በአመራርነትና በአባልነት አገልግለዋል ባላቸው ላይ የግድያ፣ የእሥራትና የማሳደድ ውርጅብኝ አውርዷል፡፡ ወያኔን ክፍኛ ያስደነገጠውን ትልቁን የፖለቲካ ድርጅት ቅንጅትን አፍርሶ, የመሪዎችን የፖለቲካ ነጻነት ሸምግልና በሚል ሽፍጥ ገድቦ፤ እንኳን ለነጻና ፍትሃዊ ምርጫ መካሄድ አስፈላጊ የሆኑትን የተቋማት ጥያቄዎች ማነሳት ቀርቶ እነሆ ወ/ት ብርቱካን ሚዴቅሳን ውሸትን እውነት ካላልሽ ብሎ ወህኒ ወርውሯት እያየን ነው፡፡
- የአገዛዙ የፀጥታ ኃይል የተቃዋሚ ድርጅቶች በየጽሕፈት ቤታቸውና በየክልሉ ያሰማሯቸውን ሠራተኞችና አስተባባሪዎች በገንዘብ በመደለል፤ በማስፈራራትና ከዚያም አልፎ በማሠር ድርጅቶችን ያለ አደራጆች ለማስቀረት በየቀኑ ወንጀል እየፈጸመ ነው።
- ለተቃዋሚዎች ቤትን የሚያከራይ ማስጠንቀቂያና እንግልት ሲደርስብት፤ ይህንንም እየፈራ ቤቱንና የመሰብሰቢያ ቦታዎችን ለተቃዋሚዎች አናከራይም የሚለው ባለ ሀብት ቁጥር በየጊዜው እየጨመረ ነው።
- ተቃዋሚዎች በየጊዜው ለሚጠይቁት ሕዝብን በአደባባይ የመሰብሰብ ጥያቄ በየምክንያቱ «አይቻልም» የሚል ምላሽ መስጠት የተለመደ ነው። በዚህ ተደጋጋሚ ክልከላ ሳይሰላቹ በጥያቄ ብዛት ስብሰባ በተወሰነ ቦታ የሚፈቀድላቸው ተቃዋሚዎች ደግሞ የተሰበሰበውን ሕዝብ ለማሸማቀቅና ከዚህ በፊት እንደታየውም ለስለላ ሥራ ለማዋል የመንግሥት "ጋዜጠኞች" ስብሰባውን ከመጀመሪውያ እስከመጨረሻው፣ በእንያዳንዱ ተሰብሳቢ ፊት ላይ እያነጣጠሩ በቪዲዮ ይቀርጻሉ። *(እነዚህ "ጋዜጠኛ" ተብየዎች የቀዱትን ስብስባ ለአንዷት ሰከንድ እንኳ በመገናኛ ብዙሃን ሲያሰሙት አይታይም።)*
- የታወቁ የተቃዋሚ ድርጅቶችን የከፍተኛ አመራር ስብስባ ሂደቶችን የመንግሥት የስለላ ቡድኖች በተደበቁ ኤሌክትሮኒክስ መቅጃዎች በመቅረፅ፣ በስለላ ክፍሉ በነፃ ጋዜጣ ስም በተቋቋሙ ጋዜጦች ለሕዝብ በማቅረብ በተቃዋሚ መሪዎች መካከል አለመተማመንን ለመፍጠርና ከዛም አልፎ የተቃዋሚ መሪዎችን በሕዝብ ፊት ደካማ አድርጎ ለማሳየት አገዛዙ ሥራዬ ብሎ ተያይዞቷል።

በሌላ በኩል ደግሞ ወያኔ ከፖለቲካ ፓርቲዎች ባላነሰ ሁኔታ ለዲሞክራቲክ የፖለቲካ ሕይወት እስትንፋስ የሆኑትን የሲቪኽ ማህበራትንና የነፃ ፕሬስን ለማዳካም ከወሰዳቸው እርምጃዎች በትንሹ የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል፤

- የስቪክ ማኅበራትን ነፃና ገለለተኛ አሠራር ጨርሶ የሚያጠፉ ሕግ እንደ ሎሌው በሚያዘው ፓርላማ አማካኝነት ደንግጓል። በተመሳስይ ሁኔታም ወያኔ የነፃ ፕሬሱ ሕዝቡን የሚያገለግልበትን መንገድ በሕግ አጥሯል፡፡
- በቅርቡ ደግሞ ይባስ ብሎ ሕዝቡን የማሰብ ነፃቱን እንኳን የሚጻረር "ጸረ-ሽብርተኛ" የተሰኘ ሕግ በእዛው የመለስ መሃተም ሆኖ በሚገለግለው ፓርላማ አጸድቋል።
- ይህም ሳይበቃው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዓይነተኛ ወያኔን መቃወሚያ የሆነውን ሰንደቃላማውን ማውለብለብ እንኳን ሕገ-ወጥ የሚያደርግ ሕግ በአሁኑ ሰዓት እያረቀቀ ነው። (ክፍል 3 ሳምንት ይቀጥላል)

## በኢትዮጵያ ያለው የሰብአዊ መብት አፈና እየከፋ እንደሚሄድ ይጠበቃል ተባለ

ሌስሊ ሌፍኮው የተባሉት እና ሂውማን ራይትስ ዋች የተባለው አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅት ተመራማሪ የሆኑት ሴት፤ ሐሙስ ሰኔ 10፤ 2002 ቀን በአሜሪካ ኮንግረስ ወይም የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርበው ባቀረቡት ምስክርነት ኢትዮጵያ በዴሞክራሲያዊ ሂደት ውስጥ አይደለችም ብለዋል።

በምክር ቤቱ የአፍሪካ ጉዳይ ንኡስ ኮሚቴ ፊት የቀረቡት ሌፍኮው፥ ከግንቦት 15ቱ የምርጫ ተውኔት በፊት በሲቢል ማህብረሰቡና በገለልተኛ አካላት ላይ የተደረገው ጥቃት ወደፊትም እየከፋ የሚቀጥል ጉዳይ እንደሆነና ይህም የኢትዮጵያን ጓደኞች ሊያሳስብ የሚገባ ነው ብለዋል። ገዢው ፓርቲ በቅርቡ አግኝቼዋለሁ የሚለው ድል የተመሰረተውም አገዛዙ ላለፉት አምስት አመታት የፖለቲካ ምህዳሩን ለመዝጋት በተከተለው ስልት ላይ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ሌስሊ ሌፍኮው፥ ገዢው ፓርቲ ህጋዊ እና አስተዳደራዊ እገታዎችን በመገናኛ ብዙሃን፣ በተቃዋሚ ፓርቲዎች እና ሲቢል ማህበረሰቡ ላይ በማኖር፤ የሲቢል ማህበረሰቡን እና ተቃዋሚ ፓርቲ አባላትን በማስፈራራት፤ እንዲሁም በተቃዋሚ ፓርቲ አባላት ላይ ቀጥተኛ ጥቃት እና እስር በመፈጸም ያለፉት አምስት አመታት ዘመቻውን እንዳካሄደም ተናግረዋል።

በምስራቅ አፍሪካ ጉዳዮች ላይ ምስክርነቶችን ለመስማት በተዘጋጀው በዚህ ስብሰባ ላይ ሌሎችም ተናጋሪዎች የተገኙ ሲሆን፤ የኮንግረሱ የጥናት አገልግሎት ባልደረባ የሆኑት አቶ ቴድ ዳኜ፥ "የ2002ቱ ምርጫ ኢትዮጵያ ወደ አንድ ፓርቲ አገርነት እየሄደች መሆኗን በግልጽ ያሳየ ነው" ብለዋል።

### የመኢዴአፓ ሊቀመንበር ለነጻነት የሚደረገውን . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

አቶ ጸጋ ስላሴ ቀደም ብሎ ከ 1987 ዓ.ም ጀምሮ የግል እጩ ተወዳዳሪ በመሆን በኢትዮጵያ የፖለቲካ ትግል ውስጥ ተሳትፎ የነበራቸው መሆኑን በዚሁ ቃለ ምልልስ የገለጹ ሲሆን በተለይም በ1997ቱ የምርጫ ሂደት በኢትዮጵያ የደረሱት ችግሮች እንዲሁም አሁን በሊቀመንበርነት እያገለገሉት የነበረውን መኢዴፓን በመወከል በነበራቸው የምርጫ ተሳትፎ ሂደት ውስጥ ያጋጠሙዋቸው ፈተናዎች በተለይም በምርጫ ፉክክር ተብየው በገዢው ፓርቲ ላይ የሰነዘሯቸው አስተያየቶች ከወያኔ ባለስልጣናት ማስፈራሪያ የደረሳቸው እንዲሁም እስራትና ማዋከብ የተፈጸመባቸው መሆኑን ገልጸዋል። በመቀጠልም ባላቸው የፖለቲካ አቋም ብቻ የግንቦት ሰባት አባል ነህ ተብለው ከፍተኛ ወከባ የደረሰባቸው በመሆኑና አካሄዱም ለበለጠ አደጋ እንደሚዳርጋቸው በማመን ኢትዮጵያንና ፓርቲያቸውን ጥለው ለመሰደድ መገደዳቸውን ገልጸዋል።

በመጨረሻም በኢትዮጵያ ውስጥ የወያኔን አገዛዝ በሰላማዊ ትግል በተለይም በምርጫ ከስልጣን ማስወገድ ፍጹም የማይታሰብ በመሆኑና ነጻነታቸውን አጥተው መኖርም ፍላጎታቸው ባለመሆኑ ለነጻነት እየተፋለሙ ካሉ ሃይላት ጋር ለመታገል ውሳኔ ላይ መድረሳቸውን ነገር ግን ከየትኛው ግምባር ጋር ለሚለው ጥያቄ በቅርብ ቀን እንደሚያሳውቁም አክለው ገልጸዋል።

### ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ባለፉት . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ስለጉዳዩ የተጠየቀው በረከት ስምኦን ጋዜጠኛዋ "የኦብነግን ሰዎች ስትፈልግ" ነበር ያለ ሲሆን፤ እሷም በበኩሏ "ኢትዮጵያ ውስጥ ሰዎችን ማናገር ወንጀል መሆኑን አላውቅም ነበር" ብላለች። ጋዜጠኛዋ ሐሙስ እለት ከኢትዮጵያ እንድትወጣ መደረጉ ታውቋል።

ባለፈው የፈረንጆች አመት በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን በተለያዩ አገራት የፖለቲካ ጥገኝነት መጠየቃቸው ታወቀ

እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር በ2009 አመት ምህረት 42500 ኢትዮጵያውያን በተለያዩ አገራት የፖለቲካ ጥገኝነት መጠየቃቸውን የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽን በሰጠው መግለጫ አስታወቀ።

ይህ ቁጥር በእርስ በርስ ጦርነት የምትታመሰውን ሶማሊያ በዛው አመት ከሸሹት ሰዎች ቁጥር በአራት ሺህ ስድስት መቶ እንደሚበልጥ ታውቋል። ከነዚህ ኢትዮጵያውያን ውስጥ 84 በመቶ የሚሆኑት ወደ ሶማሊያ፤ ደቡብ አፍሪካ እና ኬንያ ሄደዋል።

ይህ ቁጥር የተሰበሰበው ስደተኞቹ ለየሄዱባቸው አገራት መንግስታት እና ለስደተኛ ድርጅቱ የፖለቲካ ጥገኝነት ለማግኘት ባቀረቧቸው ማመልከቻዎች አማካኝነት ስለሆነ የአጠቃላይ ኢትዮጵያውያን ስደተኞችን ቁጥር አይወክልም። በያመቱ አገራቸውን ጥለው የሚሰደዱ ቁጥራቸው የማይታወቅ ኢትዮጵያውያን የፖለቲካ ጥገኝነት እናገኛለን ብለው ስለማይገምቱ በተለያዩ ሃገራት በህገወጥነት እንደሚኖሩ ይታወቃል። በተጨማሪም፥ ቁጥሩ የጉልበት ስራ ፍለጋ ወደ መካከለኛው ምስራቅ እና ሌሎች አገራት በህጋዊ መንገድ የሚሄዱትን የኢኮኖሚ ስደተኞች አያካትትም።

የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያ ያለው የኢኮኖሚ ሁኔታ እየተሻሻለ እና አገሪቱ ወደ ዴሞክራሲ እየሄደች መሆኑን ደጋግሞ ቢናገርም፤ በአስርት ሺሆች የሚቆጠሩ ዜጎች በየአመቱ አገራቸውን እየጣሉ መሰደዳቸው አገዛዙ የሚለው ተቃራኒ እውነት ለመሆኑ ምስክር ነው ሲሉ የፖለቲካ ተንታኞች ይናገራሉ።

## የግንቦት 15ቱን የምርጫ ተውኔት ተከትሎ ለወያኔ ካድሬዎች በሚደረጉ ድግሶች የህዝብ ገንዘብ በገፍ እየፈሰሰ መሆኑ ታወቀ

ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ በግንቦት 15ቱ የምርጫ ተውኔት አሸናፊነቱን በማረጋገጥ ረገድ ካድሬዎቹ ለዋሉለት ውለታ ለማመስገን በተለያዩ የአገሪቱ ከተማዎች ድግስ እየተካሄደ እንደሆነና ለዚህም የህዝብ ገንዘብ ጥቅም ላይ እየዋለ እንደሆነ ታወቀ።

የግንቦት 7 ድምጽ የአዲስ አበባ ዘጋቢ አጠናቅሮ በላከው ዘገባ በድግሶቹ ላይ ቁርጥ እና ዊስኪ እንደ ልብ የሚቀርቡ ሲሆን፤ ወጪውም በህዝብ ገንዘብ እየተሸፈነ መሆኑን ምንጮች ገልጸዋል።

የአውሮፓ ህብረት የምርጫ ታዛቢዎች ቡድን ከጥቂት ሳምንታት በፊት ባወጣው ሪፖርት በገዢው ፓርቲ እና በመንግስት መካከል ያለው ልዩነት እንደማይታወቅ እና ወያኔ የመንግስትን ንብረት ለፓርቲ ስራ እያዋለ እንደነበር መመስከሩ ይታወቃል።

የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ከሁለት ሳምንታት በፊት ባወጣው ዘገባ ገዢው ፓርቲ ዩኒሴፍ ከተባለው ግብረሰናይ ድርጅት ለእርዳታ የተቀበለውን ገንዘብ ለድግስ እና ለካድሬዎቹ ውሎ አበል ለመክፈል እያዋለው መሆኑን ዘግቦ ነበር።

የአዲስ አበባው ዘጋቢያችን፥ ድግሶቹን ተከትሎ ስለቀጣዩ የቀበሌና የወረዳ ምርጫ ከአሁኑ ውይይት መጀመሩን በላከው መረጃ አክሏል።

### የወያኔ አገዛዝ በቻይና መንግስት እርዳታ ኢሳት . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

አገዛዙ በሚፈጽማቸው የሚድያ አፈና ተግባራት የኢትዮጵያ ህዝብ አማራጭ የመረጃ ምንጭ እንዳይኖረው በማድረግ የዜናችን መሰረታዊ መብት ከመጣሱ በተጨማሪ፤ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች በየአመቱ በሚራቡባት አገር አሁንም ከፍተኛ መጠን ያለውን የህዝብ ገንዘብ አላግባብ እያፈሰሰ መሆኑን አስመስክሯል።

ከቻይና በብድር የገባው የማፈኛ መሳሪያ እስከ 700 ሜጋ ዋት ድረስ የኤሌክትሪክ ሃይል የመጠቀም አቅም እንዳለው አዲስ ነገር በዘገባው አስታውቋል። 281 ሚሊዮን ዩሮ ወይም ከ4.7 ቢሊዮን ብር በላይ የወጣበት የግልገል ጊቤ ቁጥር ሁለት ግድብ የኤሌክትሪክ ሃይል የማምረት አቅሙ 420 ሜጋ ዋት እንደሆነ ይታወቃል። ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ከውጭ የሚተላለፉ የራድዮ ስርጭቶችን እና ድረ-ገጾችንም እንደሚያፍን የሚታወቅ ሲሆን፤ በተለይ የሬድዮ ስርጭቶችን ለማፈን ከፍተኛ መጠን ያለው የህዝብ ገንዘብ ሲያፈስ ቆይቷል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 ሰዓት እስከ 3:30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2:30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፤ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org